# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 65 ነሐሴ 7 ቀን 2001 ዓ.ም

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

## መጪውን የ2002 ምርጫ አስመልክቶ ከግንቦት 7 ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ ሐምሌ 23 ቀን 2001

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የአገራችን ሁለንተናዊ ችግሮች በዋንኛነት ከመልካም አስተዳደር እጦት ጋር የተያያዙ ችግሮች ናቸው ብሎ ያምናል፡፡ መልካም አስተዳዳር ደግሞ የፖለቲካው ሥርዓት ብሉሽነት ውጤት ነው፡፡ ለዚህም ነው የግንቦት7 ንቅናቄ ብቸኛ አላማ የፖለቲካ ችግራችን በማቃለል ላይ ያነጣጠረ የሆነው፡፡ የወያኔ የዘረኛ ፖለቲካና በአንድ ዘር ላይ የተመሰረተ የዘረፋና የአድሎ አገዛዝ ይዟቸው የመጡት ሃገር አውዳሚ አደጋዎች ጤነኛ ያልሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ውጤቶች ናቸው፡፡ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ስቃዮቻችን፣ የፍትህ እጦትና የመብት ረገጣ ያስከተሉብን የስብእና መዋረድ የብልሹ የፖለቲካ ሥርዓት ውጤቶች ናቸው፡፡ ቀደምቶቻችን ለነጻነታችን የከፈሉት የደም መባ ከንቱ ሆኖ ቀርቶ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ነጻነታችንን ተገፈን በገዛ ሃገራችን የዘረኞች ባርያ ሆነን፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣ ጀግኖች በህይታቸው ያስከበሩትን ባንዲራ የማውለብለብ የዜግንት ብቻ ሳይሆን አሁንማ የማሰብና የሰውነት መብታቻችን ጭምር ጥቂት ዘረኞች ሊገፉት የቻሉት ብልሹ የፖለቲካ ሥርአት በሃገር ላይ በመንገሱ ነው፡፡ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች የመብት ጥያቄዎች፣ በየክልሉና በማእከላዊ መንግስቱ አስተዳደር ውስጥ በነጻነትና በእኩልነት ለመሳተፍ ለዘመናት የከፈሉት መስዋእትንት መና ሆኖ የቀረው በተበላሸው የፖለቲካ ሥርአታችን ምክንያት ነው፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ችግሮች ለመገላገል የሃገሪቱን ፖለቲካ አሁን የቆመበትን ዘረኛ አምባገነናዊ መሠረት አፍርሶ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መደላድል ላይ ማስቀመጥ ይኖርብናል ብሎ የግንቦት7 ንቅናቄ ያምናል፡፡ ይህንን እምነቱን ደግሞ ደጋግሞ ገልጾዓል፡፡

ግንቦት 7 "ዴሞክራሲያዊ ሥርአት" ሲልም ህዝብ በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ መርጦ ለሥልጣን ያበቃው በዚህ የተነሳ ለሕዝብ ተጠያቂ የሆነና ሕዝብን የሚፈራ መንግሥት፤ ለተወሰነ ግዜ መንግሥታዊ ስልጣኑን በኮንትራት የተረከበበት የፖለቲካ ሥርዓት ማለቱ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ የፖለቲካ ሥርዓት ግን ዝም ብለን ስለተመኘነው የሚመጣ አይደለም፡፡ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርአት ዝም ብሎ በራሱ አይከሰትም፡፡

ሁሉም በሃገሪቱ የሚገኙ ዜጎችና የእነዚህን ዜጎች ፖለቲካዊ ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ፍላጎቶች እንወክላለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በእኩልነትና በነጻነት ተንቅሳቅሰው፤ በነጻነት ተደራጅተውና አደራጅተው፤ በነጻነት የድርጅቶቻቸውን መርሃ ግብር ለህዝብ አቅርበው፤ ህዝብም በነጻነት ድምጹን ሰጥቶ፤ ህዝብ የሰጠውም ድምጽ ያለምንም ማጭበርበረ ተቆጥሮ፤ አብዛኘው ህዝብ ድምጹን የሰጠው ወይም የሰጣቸው ድርጅቶች በተናጠል ወይም በጋራ የመንግስት ሥርዓቱን ሲረከቡ ብቻ ነው ይህ ሥርዓት የሚመጣው፡፡

ነጻና ፍትሃዊ በሆነ፣ ምንም አይነት ጭቅጭቅ በሌለበት የምርጫ ሂደት በአብዛኛው ህዝብ የድምጽ ብልጫ የሚመሰየም መንግሰት እራሱን ዴሞክራሲያዊና ህጋዊ መንግሥት ብሎ መጥራት ይችላል፡፡ በህዝብ ይሁንታ የተመሠረተ መንግሥት በመሆኑም የመረጠውን የአብዛኛው ህዝብ ድጋፍ ይኖራል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ በምርጫ አሸንፎ ስልጣን ለመያዝ ለቻለው ድርጅት ወይም ድርጅቶች ድምጽ የሰጠው ህዝብ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚውንም የመረጠው ህዝብ ድጋፉን ይሰጠዋል፡፡ ሥልጣን ላይ የወጣው መንግሰት በጠምንጃ ወይም በተጭበረብረ ምርጫ ሳይሆን ነጻና ፍትሃዊ በሆነ ምርጫ የመጣ እንደሆነ ስለሚያውቅ የመረጠው ድርጅት ባለመሸነፉ የተከፋው ተቃዋሚ የተሸነፈበት የምርጫ ህግና ሂደት ፍትሃዊ መሆኑን ስለሚረዳ ሽንፈቱን በጸጋ ይቀበላል፡፡ በዴሞክራሲ ምርጫ ስልጣን ላይ የወጣው አካል የመረጠውን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ያልመረጠውን ህዝብ በእኩልነት የማስተናገድ ህገ መንግስታዊ ግዴታ እንዳለበት ስለሚያውቅ ለተቃዋሚ ድምጽ የሰጠው ህዝብ የብቀላ ፍራቻ አይገጥመውም፡፡ ተቃዋሚው ድርጅት ሆነ ዜጋ ወደፊትም በተወሰነ ግዜ የሚመጣ ሌላ የምርጫ እድል እንደሚኖር ያውቃል፡፡ ስለሚያውቀም ባለፈው ምርጫ ለድል ያልበቃባቸውን ምክንያቶች መርምሮና ማስተካካል የሚገባወን አስተካካሎ በመጪው ምርጫ አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ ተግቶ ይሰራል፡፡ በትእግስት ይጠብቃል፡፡

ይህን የመሰለው በሁሉም ዜጎች ተቀባይነት ያገኘ የዴሞክራሲ ምርጫ ሂደት ሰላምና መረጋገት ያመጣል፡፡ በሰላምና መረጋገት ላይ የተመሰረተ ጠንካራና ፈጣን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ እድገትና ግንባታ ማስጀመር የሚቻልበት ቁልፍ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ለዚህም ነው ግንቦት7 ሁሉም ዜጎች መብታቸውና ነጻነታቸው ተከብሮ ሁሉም በምርጫው የጨዋታ ህግ ተስማማተው በገቡበት የምርጫ ሂደት የሚፈጠር ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርአት በሃገራችን እንዲኖር ማድርግ አቢይ ጉዳይ ነው የሚለው፡፡

በሃገራችን እንዲህ አይነቱ የምርጫ ሙከራ ለመጀመሪያ ግዜ የተደረገው በ1997 ዓ.ም የምርጫ ወቅት ነበር፡፡ በ1997 የተደረገውን አገራዊ ምርጫ "ሙከራ"

**ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

## በግንቦት 7 መሪዎች ላይ የጥፋተኝነት ብይን ተሰጥቶ ሌሎቹን ተከላከሉ ማለት የመለስ ዜናዊ ቀጥታ ጣልቃ-ገብነት ውጤት ነው ተባለ

በግንቦት 7 መሪዎች ላይ ስለተሰጠው የጥፋተኝነት ብይን አስተያየት እንዲሰጡ የተጠየቁ አንድ የህግ ባለሙያ ‹‹ሌሎቹ ተከላከሉ መባሉ እንጂ የግንቦት 7 መሪዎች ጥፋተኞች ናቸው መባሉ አስገራሚው አይደለም፤ ከወያኔ ፍትህ አይጠበቅምና ይኸ አላስገረመኝም›› ካሉ በኋላ ‹‹ይልቁንስ በጣም የገረመኝ ሩቅ ያሉት ጥፋተኞች ተብለው እመዳፋቸው ውስጥ ባሉት ላይ ምን የተለየ ብይን ሊሰጥ ይችላልና ነው ተከላከሉ የተባሉት?›› ሲሉ አግራሞታቸውን ገልፀዋል።

በተያያዘ ዜና በአማራ ክልል የተለያዩ ወረዳዎች የተሰበሰበ የሕዝብ አስተያየት የብአዴን አባላት ከወያኔ ሎሌነት ነፃ መውጫ መንገድ ያሳዩትን ፋና ወጊ የሆኑትን ታሳሪዎችን አርዓያነት እንዲከተሉ ሕዝብ በጥብቅ ይፈልጋል። አስተያየት ሰጪዎች የብአዴን አባላት ወያኔን በመታገል ያስቀየሙትን ሕዝብ የመካስ እድል ማስመለጥ እንደሌለባቸው በአፅንዖት ገልፀዋል።

**ወደ ገጽ 2 ዞሯል**

## የአዜብ መስፍን "የኢትዮጵያ የሴቶች ማኅበራት ፌዴሬሽን" ሊቀመንበር ሆና መመረጥ በሴቶች ትግል መሳለቅ ነው ተባለ

"አዜብ መስፍን 'የኢትዮጵያ የሴቶች ማኅበራት ፌዴሬሽን' ሊቀመንበር ሆና ተመረጠች መባሉ ራሱ በሴቶች ትግል መሳለቅ ነው" ሲሉ አንድ ስማቸው እንዲገለፅ ያልተፈለገ የግንቦት 7 አባልና ለዓመታት በሴቶች መብቶችና ስነ ፆታ ላይ ጥናት ያደረጉ ባለሙያ ሴት አጋለጡ።

እንደባለሙያዋ ገለፃ ወያኔ ስለሴቶች መብት ያለው ግንዛቤ አሳፋሪ ነው። ወያኔ በሴቶች ላይ ያለው ስር የሰደደ ንቀት ምን ያህል የከፋ እንደሆነ **ወደ ገጽ 3 ዞሯል**

## ግንቦት 7 አባሎቹ ላይ የወያኔ ፍርድ ቤት ያስተላለፈው ብይን "ቧልት" ሲል አጣጣለው

በአለቀ እድሜው በመደናበር ላይ የሚገኘው የፈላጭ ቆራጩና የዘረኛው መለስ አገዛዝ እንደፈለገ በሚያሽከረክረው የይስሙላ ፍርድ ቤት በግንቦት 7 መሪዎች ላይ የጥፋተኝነት ብይን አስተላልፏል።

የዘረኛው መለስ አገዛዝ ‹‹ሊገድሉን ሲሉ ደረስንባቸው፤ ህገመንግስቱንም ሊያፈርሱ ሲሉ ያዝናቸው›› እያለ የአድማጭ ጆሮ ለማግኘት ቢያላዝንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ‹‹እሰየው፣ አድርገውት ነው!!!›› ከሚል ምላሽ ውጭ ወያኔዎች እንዳሰቡት የደገነገጠ አልተገኘም። እንዲያውም ዘረኛው መለስና ተላላኪው በረከት በየቀኑ እንደልባቸው በሚፈነጩበት ቴሌቪዥን የእነ ጄኔራል ተፈራ ማሞን ስም በተጠራ መጠን ሕዝብ ይበልጥ እያደነቃቸውና እየደገፋቸው እንደሄደ ለማወቅ ተችሏል።

ከጊዜ ወደጊዜ እየተጠናከረ በመጣው ፀረ-ወያኔ ተቃውሞ አገዛዙ ተስፋ እየቆረጠ በመጣ ቁጥር ሰዎችን በሃይል ለመግዛት የሚያደርገው ሙከራ በዚያው ልክ የአገዛዙን እድሜ እያሳጠረው ሲሆን፣ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ከተነሱ በሞት አፋፍ ላይ የሚገኘውን ብካይ ሥርዓት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማስወገድ እንደሚችሉ በርካቶች ይናገራሉ።

የወያኔ የይስሙላ ፍርድ ቤት ሐምሌ 30 ቀን የሰጠውን ብይን አስመልክቶ የግንቦት 7 ንቅናቄ ባወጣው መግለጫ የወያኔ አገዛዝ የ1997ቱን የሕዝብ የምርጫ ውሳኔ በአመጽ ገልብጦ በመፈንቅለ ህዝብ ውሳኔ ስልጣን ላይ የተከመረ አገዛዝ ነው ብሎ እንደሚያምን ገልፆ ይህ ህገወጥ አገዛዝ ለፈጠራቸው ማናቸውም ተቋማት ግንቦት 7 እውቅና እንደማይሰጥ አስታውቋል፡፡ ይህ አቋሙም የወያኔን የፖለቲካ ፍላጎት ከማስፈጸም ውጭ ሌላ የህልውና ምክንያት የሌላቸወን ፍርድ ቤቶችንእንደሚያጠቃልል በመግለጽ በወያኔ የቁጭ ይበሉ ፍርድ ቤት የተላለፈውን ውሳኔ ‹‹ቧልት›› ሲል አጣጥሎታል። በመጨረሻም ግንቦት 7 የወያኔን ዘረኝነት በመቃወማቸው አሁን በእስር ላይ ለሚገኙት ጀግኖች በሙሉ ያለውን አድናቆት ገልጿል።

## የወያኔን የፍርድ ቤት ተረት ለወያኔ አጋፋሪዎች ትተን ወገኖቻችንን እንታደግ፤ ሃገራችንን ከጥፋት እናድን!

ፍትህ በወያኔ መዳፍ ውስጥ እንደገና ስትደፈጠጥ ታየ። የሚናገሩትን በጥንቃቄ እንዲያጠኑ የተደረጉ የሰው ምስክሮችን፣ ከኢንተርኔት የተቀዱ ድምፆችንና ወረቀቶችን በማስረጃነት ተቀብሎ ፍትህን ለማዋረድ የተቋቋመው የወያኔ ፍርድ ቤት በጥቂት የግንቦት7 አመራር አባላትና እራሱ ወያኔ የግንቦት7 አመራር አድርጎ በሰየማቸው ሌሎች ግለሰቦች ላይ በሞት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል የጥፋተኝነት ብይን ሰጥቷል፡፡

ይኸው ጉደኛ ፍርድ ቤት እነዚሁ አስራ ሶስት ሰዎችን ጥፋተኞች ናቸው ባለባቸው ወንጀሎች ሌሎች ሃያ ስምንት ሰዎች የቀረቡባቸውን ክሶች እንዲከላከሉ ብይን ሰጠ።
የሚገርመው በዚህ ብይን ውስጥ ያለው ቧልት ነው፡፡ ይከላከሉ የተባሉት ተከሳሾች ክሱን በአጥጋቢ ሁኔታ ከተከላከሉ በገንዝብና የቁሳቁስ እርዳታ የተከላካዮቹን የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ደግፈዋል ተብለው በግንቦት7 አመራር አካላት ላይ በጥድፊያ የተሰጠው የጥፋተኛነት ብይን ምን ሊውጠው ነው? ፍርድ ቤቱ የሰጠውን የጥፋተኛነት ውሳኔ ሊሽር ነውን? ወይስ ፍርድ ቤቱ ተከላከሉ ያላቸው ተከሳሾቹ ክሱን አይከላከሉም የሚል ስሌት አስቀድሞ ሰርቷል? ወይስ ቢከላከሉም ባይከላከሉም እነሱንም ጥፋተኛ የሚያደርግ ብይን አስቀድሞ በኪሱ ይዞ ተቀምጧል? በፍትህ ላይ ቧልት ይሏል ይህ ነው፡፡

ከወያኔ ፍትህ የማንጠብቅ ቢሆንም የአገራችን የፍትህ ሥርዓት በመዝቀጥም አልፎ ብይን በስልክ ሲነገራቸው የተሰየሙበትን ችሎት ጥለው የሚነሱ ዳኞችን አለማየታችን እያስገረመን ነው። መቸ ነው የወያኔ የህግ ባለሙያዎች በአሻጉሊትነት እያገለገሉት ያለው ሥርዓት እነሱንም እንደማይምር የሚረዱትና በጋራ ለህግ ልዕልና ጥብቅና የሚቆሙት? መቼ ነው ለገንዘብና ለጉልበት ጣዖቶች መስገድ አቁመው፣ ለፍትህ ክቡርነት ከሚታገሉቱ ጎራ ቆመው የሚቆጠሩት?

ሆኖም ወያኔን በማገልገል ላይ ካሉት የህግ ባለሙያዎች ያጣነውን ጀግንነት ሃገራቸውንና ወገናቸውን ከሚወዱ በወያኔ የወታደራዊና የአስተዳደር ተቋማት ውስጥ ከሚሰሩ ዜጎች እያገኘነው ነው። የወያኔን ዘረኝነትና ዘራፊነት በመቃወም በብአዴን ኮታ ሠራዊቱን የተቀላቀሉ የጦር መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች «እስከ ዛሬ የአማራ ሕዝብ ለወያኔ ዘረኞች በባርነት እንዲገዛ፤ ለወያኔ ሃገራዊ ክህደትና ዘረፋ ሽፋን ሰጪ ሆነን የኖርንበትን አሳፋሪ ታሪክ በደማችን እናጸዳዋለን» ብለው ተነስተዋል፡፡ ይህ የሠራዊቱ ቁጣና ምሬት የወያኔ ግፍና ውርደት ገፈት ቀማሽ በሆነው የአማራ ሕዝብም ውስጥ እየተንቀለቀለ ነው፡፡

የተጀመረው ከወያኔ አገልጋይነት ነፃ የመውጣት ትግል አሁን በእስር እየተንገላቱ ያሉ ጀግኖችን አፍርቷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእነዚህ ጀግኖች ትልቅ አክብሮት አለው። የወያኔ አሽከር ከመሆን የባሰ ውርደት፤ ከዚያ የባሰ የህሊና ቁስል ባለመኖሩ አካላዊ ጉዳት ቢደርስባቸውም በመንፈሳዊ ነፃነት ተክሰዋል። የጀግኖቻችን አርዓያነት ሌሎች ብዙዎችን እየቀሰቀሰ እንደሆነ እናውቃለን። የጀግኖቻችን አርዓያነት ትግላችንን በበለጠ እልህና ጥንቃቄ እንድንቀጥል አበረታቶናል። የነፃነት ደወል ከብአዴን ወደ ኦህዴድና ደህዴድ መንደሮች ዘልቆ እየተሰማ ነው፡፡ ወደ ሶህዴፓ፣ አብዴፓ እና ሌሎችም እንደሚዳረስ እናውቃለን። በየቦታው አመፃ እፈነዳዳ ነው። ህሊናቸው የሸጡ ጥቂት የወያኔ ምስለኔዎች በግዴታ ከተሰባበሱ አባሎቻቸው እየተነጠሉ ነው። ወያኔ መላውን ኢትዮጵያ አስሮ መዝናናት እንደማይችል የሚታይበት ቀን በፍጥነት እየመጣ ነው፡፡

ነፍስና ሥጋቸውን ለወያኔ ከሸጡ ጥቂት የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች መሪዎች በስተቀር ማንም ለራሱ፣ ለቤተሰቡ፣ ለወገኑና ለሃገሩ ክብር ያለው ዜጋ ዓይን ያወጡ ዘረኞች፣ ዘራፊዎችና ሃገር ከሃዲዎች አሽከር መሆን ቀርቶ በአቻነት ደረጃ እንኳን ለመስራት ፍላጎቱ እንደማይኖረው እናውቃለን፡፡ ወያኔ ዛሬ አለኝ የሚለውን የአባላት ብዛት እንዴት እንዳሰባሰበው እናውቃለን፡፡ ወያኔ ብቸኛው መንግሥታዊና የግል ቀጣሪ በሆነበት ሃገር ዜጎችን በልጆቻቸውና በአረጋዊ ተጧሪ ወላጆቻቸው ጉሮሮና እንጀራ በማስፈራራት አስገድዶ ሚሊዮኖችን የአባልነት ፎርም እንዳስሞላ እናውቃለን፡፡ ወያኔ ብዙዎችን በስለላና በአፈና ተቋማቱ በማስፈራራት አባል እንዳደረጋቸው እናውቃለን፡፡ ሰው በዜግነቱ ማግኘት የሚገባውን መብት፣ ጥቅም፣ የኑሮና የሥራ ዋስትና የወያኔ ጀሌ ካልሆነ የማያገኝበት ሁኔታ በመፍጠር ወያኔ በመቶሺዎች የሚቆጠሩትን ዜጎች የፖለቲካ አስገድዶ መድፈር እየፈጸመባቸው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

የግንቦት 7 ንቅናቄ ከዚህ ቀደምም እንዳለው በእነዚህ አዋራጅና አሳፋሪ ሁኔታዎች ወያኔ አስገድዶ የሰበሰበው አባል ቀን ጠብቆ መልሶ ወያኔ ላይ ለመፈንዳት የተጠመደ ፈንጂ ነው፡፡ ስለዚህም ነው የግንቦት ንቅናቄ «በብአዴን፣ በኦህዴድ፣ በደህዴድና በሌሎችም ወያኔ ‹አጋሮቼ› በሚላቸው ድርጅቶች ውስጥ አፍኖ የያዛችሁ ወገኖቻችን ስቃይ ይሰማናል» የሚለው፡፡ እናንተም እንደ ወንድሞቻቸሁ እንደነ ጄኔራል ተፈራ ማሞ፣ እንደእህታችሁ እንደ ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ በቅርቡ ለነጻነታችሁ የምትነሱበት ቀን እንደሚመጣ የግንቦት7 ንቅናቄ ጥርጣሬ የለውም፡፡

በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንም ሃገራችንንና ወገናችንን ከዘረኞች ለመገላገል የተጀመረው ትግል ከግቡ ሳይደርስ እንደማታርፉ እናውቃለን፡፡ በወያኔ ጅራፍ እየተገረፉ ዘግናኝ ሰቆቃዎች እየተፈፀመባቸው ስላሉት ወገኖቻችን እናንተም እየቆሰላችሁ ነው፡፡ እነዚህ የዛሬዎቹ ጥቂት ታጋዮቻችን ያቀጣጠሉት ችቦ እንዲንቦገቦግ የሚቻላችሁን እንደምታደርጉ በተግባር እያሳያችሁ ነው፡፡ በዚህ ተግባር ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ዛሬ በእስር የሚማቅቁ ወገኖቻችን ለነጻነታችን ሲሉ ሜዳ ላይ የበተኗቸውን ቤሰቦቻቸውን መታደግ መሆኑን ልናስታውሳችሁ እንወዳለን።

በወያኔ እስር ቤቶች ውስጥ አስከፊ ሰቆቃ እየተፈፀመባችሁ ላላችሁ ወገኖቻችን መልእክታችን ይድረሳችሁ። የቆማችሁለት ሃገርን ከዘረኛው ወያኔ ነፃ የማውጣት ትግል ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ዛሬ ከትናንቱ በበለጠ በርካቶች የታሰራችሁለትን ትግል ተቀላቅለዋል። የእናንተ መስዋዕትነት የቤተሰቦቻችሁና የልጆቻችሁ ስቃይ የድላችንን አይቀሬነት እያበሰረ ነው።

ለዘረኛው ወያኔ ለራሱ ደግሞ እንዲህ እንለዋለን፡፡ «በፍትህ ለመቀለድ፤ በሰው ስቃይ ለማሾፍ፤ በሃገር ክህደት ለመክበር እና በዘረኛት ለመጠቃቀም የዘረጋኸውን ባለጌና ነውረኛ ሥርዓትን ለማስወገድ ቆርጠን ተነስተናል። በመቃብርህ ላይ ነጻነት፣ ፍትህ፣ እኩልነትና አንድነት የሰመሩባት፤ ሁሉም የሃገሪቱ ዜጋ፣ ሁሉም የዘውግ ማኅበረሰብ፣ የሁሉም እምነት ተከታዮች፣ ሁለቱም ጾታዎች እና ሁሉም የእድሜ ቡድኖች የሚኮሩባትና የሚመኩባት ኢትዮጵያን እንገነባለን።»

## በግንቦት 7 መሪዎች ላይ የጥፋተኝነት ብይን . . .


### ከገጽ 1 የዞረ


በሌላ በኩል ደግሞ ለዘመናት ተፋቅሮና ተከባብሮ የኖረው የአማራና የትግራይ ህዝብ በወያኔ መሰሪ ድርጊት ምክንያት ከምንጊዜውም በላይ ሆድና ጀርባ እየሆነ መምጣቱን በክልሉ ተዘዋውሮ የተመለሰው ዘጋቢያችን ገልጿል። ዘጋቢያችን በአማራ ክልል ስላለው የሕዝብ ስሜት ሲገልፅ «ከዚህ በፊት የትግራይ ተወላጆች በክልሉ ውስጥ እንደማንኛውም የአማራ ተወላጅ በነጻነት፣ ከህዝቡም ጋር ተፋቅረውና ተሳስበው ይኖሩ ነበር፤ ከግንቦት 97 ምርጫ በሁዋላ ግን በሁለቱ ህዝቦች መካከል ያለው አለመተማመን እየሰፋ በመምጣቱ ከዚህ ቀደም የነበረው ትስስር እየላላና ወደ አደገኛ ሁኔታ እየተለወጠ መጥቶአል» ብሏል።

በአብዛኛው የክልሉ ነዋሪዎች እምነት የዚህ ችግር ምንጩ ወያኔ የአገዛዙን አፈናና ጭቆና የሚቃወሙትን ሁሉ ለመመንጠር በጊዜያዊ ጥቅም በአሽከርነት ሲገለገልባቸው የነበረው የአማራ ተወላጆች እራሳቸውንና ሕዝባቸውን በማዋረድ የሚያገኙት ጥቅም እየከነከናቸው በመምጣቱ፤ አብዛኞቹም በመጻጸት . . . በሕዝባቸው ላይ የሚፈጸመው ባርነት እንዲያበቃ ከተቃዋሚዎች ጎራ በመሰለፋቸው፤ እኛ በሥልጣን ላይ ከሌለን አማራው ተነስቶ ይፈጅሃል የሚሉትን ትግሪኛ ተናጋሪ በመደለል አማሪኛ ተናጋሪ በሆኑ ወንድሞቹ ላይ በግልጽም በስውርም በሰላይነት እንዲሰራ በማሰማራታቸው እንደሆነ በስፋት ይነገራል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ በአማራው ክልል የሚኖረው ሕዝባችንም ሆነ በተቀረው የአገራችን ክፍሎች ያለው በዚህ የወያኔ መሰሪ ተንኮል ሳይጠመድ እና ወንድሙ ከሆነው ትግርኛ ተናጋሪው ጋር በጥላቻና በቂም መርዝ ሳይለከፍ ይልቁንም የአገሪቱና የመላው የአገሪቷ ሕዝብ ዋነኛ ባላንጣ የሆነውን የመለስ ዜናዊና በዙሪያው የተሰባሰቡ ጥቂት ጸረ አገር ኃይሎች የአገዛዝ እድሜ ለማሳጠር በጋራ እንዲነሳ ጥሪውን ያቀርባል።


በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን



የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## ኢትዮጵያ ዛሬም የብሔረሰቦች እስር ቤት ናት!

ግንቦት 7 በደንቨር በጠራው ስብሰባ ላይ **በኤፍሬም ማደቦ** የቀረበ **ክፍል 1**

በቅርቡ ፕሬዚዳንት አባማ ጋናን ሲጎበኙ ከትናንሾቹ የገጠር ከተማዎች ከሳኒያኒ እስከ ቦልጋታንጋ እስከ ትላልቆቹ አክራና ኩማሲ ድረስ ጋናን ካጥለቀለቃት የወረቀትና የካርድቦርድ ብዛት በአብዛኛዉ **“We well come You “** የሚል ቃል የተፃፈበት ነበር።ለመሆኑ **“WE”** ና **“You”**ን የጋናን ህዝብና የአሜሪካዉን ፕሬዚዳንት ምን አገናኛቸዉ? ለምን በቀላሉ ዬትም ቦታ እንደሚደረገዉ **“Welcome President Obama** አላሉም? የጋና ህዝብ የቦታ ርቀት፤ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ልዩነት ወይም በመካከላቸዉ የተንጣለለዉ ሰፊዉ የአትላንቲክ ዉቅያኖስ አላገደዉም በአባማና በነሱ መካከል ያለዉን አፍሪካዊ አንድነት አርቆ ለመመልከት። እኛ ግን በህገ መንግስታዊ የጎሳ አጥር ተለያይተን እንኳን አፈሪካዊነት ኢትዮጵያዊነቱንም እንድንረሳ እየተደረገ ነዉ።

በነገራችን ላይ ዛሬ የአፍሪካ ክፍለ አህጉር የዲሞክራሲ ምልክት ተብላ የምትጠራዉ ጋና በ1957 ዓም ነፃነቷን ስትቀዳጅ ለጋና ነፃነት ከፍተኛ ትግል ካደረጉት አገሮች ዉስጥ አገራችን ኢትዮጵያ የቀዳሚነት በታ አላት። ከመጀመሪያዉ የጋና መሪ ከክዋሜ ንክሩማ ጋር ሆነዉ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን (አአድ) የመሰረት ድንጋይ ካኖሩት የአፍሪካ መሪዎች ዉስጥ ዋሳኙን ሚና የተጫወቱት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሤ ነበሩ። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተመሰረዉ አዲስ አበባ ዉስጥ ሲሆን የአአድና አአድን የተካዉ አፍሪካ ህብረት ዋና ጽህፈት ቤት የሚገኘዉ ኢትዮጵያ መዲና አዲስ አበባ ዉስጥ ነዉ። አዲስ አበባ የተመድ ኤኮኖሚክ ኮሚሺን ለአፍሪካና (ECA) የሌሎችም አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ጽህፈት ቤቶች መናኸሪያ ናት። ከዚህ በተጨማሪ የተመድ የፀጥትዉ ምክር ቤት ከኒዮርክ ዉጭ ከተሰበሰበባቸዉ ጥቂት ከተማዎች ዉስጥ አንዷ አዲስ አባባ ናት። ዛሬ ግን የመጀመሪያዉ ጥቁር አሜሪካዊ የአሜሪካ መሪ አፍሪካን ሲጎበኝ የመጀመሪዬ ብሎ የወሰደዉ የአፍሪካን የታሪክ፤የፖለቲካና፡ የዲፕሎማሲ ምልክት የሆነቸዉን ኢትዮጵያን ሳይሆን ኢትዮጵያን እንደ ታላቅ እህት የምትመለከተዉን ጋናን ነዉ። ይህ የሚያሳየን በልጆቿ ደም እጃቸዉ የቆሸሸዉን የኢትዮጵያ መሪዎች እንኳን የዲሞክራሲ አባት የሆነች አገር መሪ ግዑዟ የአዲስ አበባ መሬትም “አይናችሁን ላፈር” ካለቻቸዉ ቆይቷል።

እዚህ ዴንቨር ከመምጣቴ ከአንድ ሳምንት በፊት አንድ የሳይበር ግርግር ያገናኘን ሰዉ ደወለልኝና እናንተ ግንቦት ሰባቶች ወሬ አበቃ ብላችሁ አልነበረም እንዴ ምንድነዉ እንዳበደ ሰዉ አንዴ ለንደን አንዴ ካናዳ አሁን ደግሞ ዴንቨር- ምንድነዉ እንዲህ የሚያንቀዠቅዣችሁ አለኝ- አልተሳሳትክም አብደናል- አንተ እንደምትለዉ አልለየልንም እንጂ አብደናል! ኢትዮጵያዊ ሆኖ ያላበደ ቢኖር አንተና መሰሎችህ ብቻ ናችሁ አልኩት። እስኪ ይታያችሁ ለምን አናብድም?

ከወርቃማዉ ዘር አልተወለዳችሁም ተብለን በገዛ አገራችን ሁለተኛ ዜጋ ስንሆን ለምን አናብድም?

አገራችን በአንድ በኩል በፍጥነት እያደገች ነዉ እየተባለ በሌላ በኩል ደሞ አንድ በተሰብ ዉስጥ ታላቅና ታናሽ በፈረቃ ነዉ የሚበሉት ሲባል እየሰማን ለምን አናብድም?

*እስልምና እምነት ተከታዮች ምነዉ ሲሉ ክርስቲያኖችን ጠይቁ- ክርስቲያኖች ምነዉ ሲሉ ደግሞ እስላሞች አልተስማሙም እየተባለ ለሺ ዐመታት ተከባብረዉ የኖሩ ሐይማኖቶች ሲጋጩ እያየን ለምን አናብድም?*

EFFORT ባለቤቱ የትግራይ ህዝብ ነዉ ተጠቃሚዉ ግን ቤሳ ቤስቲን የማይጣልለት የኢትዮጵያ ህዝብ ነዉ ሲባል ለምን አናብድም?

ትናንት ከጎናችን ቆሞ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ታሪክና ህዝብ አዋርዷልና መወገድ አለበት እያለ ሲጮህ የነበረዉ ጎበዝ ዛሬ ያንን ጉብዝና ለመቶ ሺ ዶላር የከተማ ቦታና ቤት ለዉጦ “መለስ ሺ አመት ይንገስ” እያለ ሲዘምር ለምን አናብድም?

እስኪ በምናባችሁ ቀኝ እጃችሁ ላይ ኢትዮጵያን ግራ እጃችሁ ላይ ደግሞ አንድ መቶ ሺ ዶላር አስቀምጡ- የትኛዉ ነዉ ሚዛን የሚደፋዉ? አባቶች ፤ እናቶች ፤ እህቶችና ወንድሞች ለዚህ ጥያቄ የምንመልሰዉ መልስ ነዉ አገራችንን ለማጥፋት ከቆረጡ ዘረኞች ጎን ወይም አልጠፋም ብሎ ከሚታገለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ጎን የሚያሰልፈን! ዛሬ ከዚች ዉብ ከሆነችዉ ከ **mile high city** ለዚህ አይዟችሁ ለሚለን የኢትዮጵያ ህዝብና በመላዉ አለም ለሚገኘዉ የዚህ ጀግና ህዝብ አካል ለሆነዉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚከተለዉን መልዕክት በግንቦት 7 ስም ማስተላለፍ እፈልጋለሁ - ወደፊት ለመሮጥ ብሎም ለመዝለል ወደ ኋላ መንደርደር የግድ ነዉና አንዳንዴ ባለፍንበት መንገድ ከአንድ ግዜ በላይ ለማለፍ እንገደድ ይሆናል፤ ሆኖም መሆን የሚቻለዉን ነገር ሁሉ ሆነን- እሚገባበት ቦታ ሁሉ ገብተን- ማድረግ የምንችለዉን ነገር ሁሉ አደርገን- አንዳንዶቻችን እንዳባቶቻችን ዉዱን መስዋዕትነት ከፍለን ብዙዎቻችን ግን በምናፈርሰዉ የመለስ ዜናዊ ስርአት ላይ ተረማምደን ከዘረኝነትና ከጎጠኝነት ነፃ የሆነች ኢትዮጵያን እንገነባለን!

ስለድህነት ብዙ አዉርተናል ፤ ድርቅና ረሀብን ሳናነሳ ያለፍንበት ግዜ የለም፤ስለ አገራችን የምጣኔ ኃብት እድገትም ብዙ ብለናል፤ አገራችን ዉስጥ ዲሞክራሲን እንዴት እንገነባለን የሚለዉን ጥያቄ አንስተን በተለያዩ መድረኮች ላይ በሚገባ ተወያይተናል- ወገኖቼ ዛሬ ባለችኝ ትንሽ ግዜ አብሬያችሁ ልካፈል የምፈልገዉ ስለዘረኝነት በተለይም የኢትዮጵያን ህዝብ የበይ ተመልካች ስለደረገዉ ስለ ወያኔ ዘረኝነት ነዉ።

ስለዘረኝነት ስናወራ ዘረኝነት ምን ማለት እንደሆነና ምናልባትም በህይወታችን ዉስጥ ቢከሰት ምን ሊመስል እንደሚችል ሁላችንም በዉል ልናዉቀዉ ይገባል። የሰዎች ሁሉ መጀመሪያና መጨረሻ ፍፁም ተመሳሳይ ነዉ፤ወደዚህ አለም ስንመጣ ቀድመዉን የመጡ በክብር ይቀበሉናል ከዚህ አለም ስንለይ ደግሞ ከኋላችን የሚቀሩ በክብር ይሸኙናል። እኛ ሰዎች የምንለያየዉ ከልደት እስከሞት ባለዉ ግዜ ውስጥ ነዉ። ይህም ቢሆን ሀብታምና ደሃ፤የተማረና ያልተማረ፤ ሳይንትስትና ተራ ሠራተኛ፤ አዋቂና አላዋቂ፤ መሪና ተመሪ፤ለዘብተኛና ወግ አጥባቂ አድርጎ የሚያለያየን የተወለድንበት የዘር ሀረግ ወይም የቆዳ ቀለማችን አይደለም።

ለመሆኑ ዘረኝነት ምንድነዉ? ዘረኝነት ማለት ሰዎች በማህበራዊ ኑሮ ዉስጥ ያላቸዉ ቦታ የሚወሰነዉ በችሎታቸዉና በባህሪያቸዉ ሳይሆን በተወለዱበት የዘር ሀረግ ወይም የቆዳ ቀለም ነዉ ብለዉ የሚደመድሙ ሰዎች እምነት ነዉ። ሰፋ ባለ መልኩ ዘረኝነት ዘርን፣ ጎሳን፤ የቆዳ ቀለምን፣ ወይም አስተሳሰብን መነሻ በማድረግ ሰዎች መሠረታዊ ነፃነታቸዉን በፓለቲካ፣ በኢኮኖሚና፣ በማኅበራዊ ዘርፎች ወስጥ እኩል እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ ጎታች የሆነ ኋላ ቀር አሰራር ነዉ።

**ክፍል 2 በሚቀጥለው ሳምንት እናቀርባለን**

## የአዜብ መስፍን . . . ከገጽ 1 የዞረ

የራሱ የወያኔ የሴቶች ድርጅት ግንባር ቀደም መሥራች የነበሩት ወ/ሮ የውብማር አስፋው በ2001 ዓ.ም ያሳተሙት “ፊኒክስዋ ሞታም ትነሳለች - ያልተቋጨው የትግራይ ሴቶች ገድል” በተሰኘውን መጽሃፋቸው ማጋለጣቸው አስታውሰዋል።

ወ/ሮ የውብ ዳር በመጽሃፋቸው ‹‹ደርግ ተደምስሶ የሽግግር መንግስቱ ከተቋቋመ በኋላም ይሁን ህገ መንግስቱ ከጸደቀ በኋላ … የትግራይ ሴቶች ማኅበራት የድርጅቱ ተቀጥላ ሆነው እንዲሄዱ እንጂ በትግላቸው ያረጋገጡትንና ህገ መንግስቱ ያጎናጸፋቸውን በነጻነት የመደራጀት መብት ተግባራዊ ሊያደርጉ አልቻሉም። የሚያጋጥሙዋቸውን ችግሮች ተደራጅተው ራሳቸው እንዳይፈቱና ወደፊት እንዳይራመዱ እጅ ተወርች ታስረው እንዲጓዙ ተደርገዋል። ይህ አካሄድ በህወሃት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሚገኙትን የሴቶች ማኅበራት እንዴት ጠፍሮ እንደያዘ መመልከቱ ጠቃሚ ነው›› በማለት የወያኔን መሰሪነት ማጋለጣቸው ባለሙያዋ አስታውሰዋል።

ባለሙያዋ አያይዘውም “ወያኔ ስለ ሴቶች መብት የሚለፍፍ ቢሆንም ውስጥ … ውስጡን ለአባላት በሚያሰራጭ ‹ሕዝባዊ አደራ› በሚሉት መጽሄት ‹ኢህአዴግ የሁሉም ዴሞክራሲያዊ ማኅበራት መሪ ነው። በመሆኑም የሴቶችን ማኅበር ለማጠናከር ካድሬዎችን በማሰልጠንና በማስተካከል በኢንፎርሜሽንና ሪፖርት አማካይነት በማኅበሩ ውስጥ ካሉት ካድሬዎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል› በማለት የሴቶች ማኅበራት ነፃነት መደፍጠጥ ያለበት መሆኑን ለካድሬዎቹ በግልጽ ያስተምራል” ብለዋል። የኢትዮጵያ ሴቶች በነፃነት የመደራጀት መብት ምን ያህል የጠበበ እንደሆነ የኢትዮጵያ የህግ ባለሞያ ሴቶች ማኅበርንና በቅርቡ በወያኔ ወከባ ሃገራቸውና ሥራቸው ለቀው ለስደት የተዳረጉት ወ/ሮ ማህደረ ጳውሎስ በማስረጃነት ጠቅሰዋል።

የግንቦት 7ዋ ባለሙያ ‹‹ወ/ሮ የውብዳር እንዳለችው ፊኒክሱዋ ሞታም ትነሳለች፤ የኢትዮጵያ ሴቶች የወያኔዋ ቁንጮ የአዜብ መስፍንን መሰሪ ዓላማ እናከሽፋለን። የብአዴን አባላት በቅርቡ የወያኔ አፈናና ዘረኝነት በቃን በማለት ለነጻነታቸው እንደተነሱት ሁሉ የኢትዮጵያ ሴቶች በየአቅጣጫው - ከወያኔ ጉያ ውስጥ እንኳን ሳይቀር - ተሰባስበው በወያኔ ላይ ይነሳሉ። ያኔ ወዮላት ለአዜብ!!›› ሲሉ አስተያየታቸውን ደምድመዋል።

## መጪውን የ2002 ምርጫ አስመልክቶ ከግንቦት 7 ንቅናቄ የተሰጠ መግለጫ ...

ከገጽ 1 የቀጠለ

ያልንበት ምክንያት የ1997 ምርጫ በበርካታ ምክያቶች ቀድሞ ከነበሩ ምርጫዎች የተሻለ የነበረ በመሆኑ እንጂ አንድ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ማሟላት የሚገባውን ቅድመ ሁኔታዎች በሙሉ አሟልቶ የተገኘ እንዳልነበረ ስለምናውቅ ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊነቱ ታሪካዊ ነው የተባለለት የ1997 ምርጫ ገና ከጅምሩ ወያኔ በተቀናቃኞቹ ላይ የበላይነት የሚሰጡት  በርካታ ህገወጥ ድርጊቶች የተከናወኑበት ነበር፡፡ ህዝቡን ለማስፈራራት በአንዳንድ ክልሎች ከምርጫው በፊት ግድያ፣ እስራትና ወከባ በስፋት ተካሂዷል፡፡ ወያኔ ሁሉንም መንግሥታዊ የሆኑ ተቋማት ንብረት ሃብትና የሰው ሃይል በእጁ ይዞ እንዳሻው በሚያዝበትና በሚጠቀምበት ሁኔታ የተደረገ ምርጫ ነበር - የ1997ቱ ምርጫ፡፡ ምርጫው የተደረገው መለስ እንዳሻው በካድሬዎቹ ሞልቶ በፈጠራቸው፣ እንዳሻው የሚያዛቸው የምርጫ ቦርድና የፍትህ ተቋማት ቁጥጥር ሥር ነበር፡፡ ምርጫው የተደረገው ወያኔ እንዳሻው በህዝብ ላይ ሊያዘምት የሚችለውን የወታደር፣ የስላላና የፖሊስ ሃይል በእጁ እንደያዘ ነበር፡፡ ምርጫው የተደረገው በመንግሥት እጅ ባለውና ብቸኛው የአገሪቱ የመገናኛ ብዙሃን ራድዮ ቴሌቪዥኑና ጋዜጣው የምርጫው ውድድር ከመጀመሩ ከወራት በፊትና ከተጀመረም በኋላ የሚያቀርቡትን ፕሮግራምና ዜና የወያኔ የምርጫ ዘመቻ ማድርግ በቻሉበት፣ በቀን 24 ሰአት ለወያኔ አሸናፊነት በሚሰሩበት ሁኔታ ነበር፡፡ ተቃዋሚዎች ግን በወያኔ ችሮታ ተቆጥሮ በሚሰጣቸው በቀን ስድስት ደቂቃ የሚድያ ራሽን ተርበው የተከናወነ ምርጫ ነበር፡፡

አንግዲህ እነዚህንና ሌሎችንም ያልጠቀስናቸውን የወያኔን የመመረጥ ሚዛን ወደእራሱ የሚያጋድሉ ብዙ መሰሪ ሥራዎችን ሠርቶ ነበር ተቀናቃኝ የሆኑትን የፖለቲካ ድርጅቶች በዝረራ አሸንፌ እወጣለሁ በሚል ትምክህት ምርጫውን ለተቃዋሚዎች ከሌላው ግዜ ከፊት አድርጎ ኑ ግጠሙኝ ያለው፡፡ የወያኔ የፖለቲካ ሥርአት (ፖለቲካ ከተባለ) መሰረቱ የበሰበሰ የጥቂት ዘረኞችና ሙሰኞች ቡድን በመሆኑ ከምርጫው በፊት ምርጫውን ለማሸነፍ በማለት ያሴረው ሴራ በሙሉ ለድራማ ብሎ በከፈታት የዴሞክራሲ ጠባብ ቀዳዳ የሚገባውን የሕዝብ ቁጣና የተቃወሞ ጎርፍ መቋቋም አቃተው፡፡ ተቃዋሚዎች በተከፈተችው የዴሞክራሲ ቀዳዳ ተጠቀሙ፤ ሕዝብም ደገፋቸው፡፡ እናም ወያኔን በራሱ የጨዋታ ህግ፣ በገዛ ሜዳውና በራሱ ዳኘነት ገጥመው አፈር ድሜ አስጋጡት፡፡ ወያኔ ያልጠበቀው ሽንፈት ገጠመው፤ አፈረ፡፡ እንደ ሕፃናት ጨዋታ “ዳቦ ተቆረሰ ጨዋታ ፈረሰ” ወደነበራችሁበት ተመለሱ ሂዱ ሂዱ ብሎ ተቃዋሚዎቹንና ሕዝብን አመናጨቀ፡፡ ይህ አይሆንም ያሉትን ቀድሞውኑ ሙሉ በመሉ ተቆጣጥሯቸው በነበሩት ጠፍጥፎ በሠራቸው ተቋናት ውስጥ ባሰባሰባቸው ጭራቆች አመካይነት ዘመተባቸው፡፡ የመገናኘ ብዙሃኑ የጭጋ ጅራፉን፣ ዳኞች የሃሰት ብይናቸውን፣ አጋዚዎች ጥይታቸውን በሕዘብና በተቃዋሚ ላይ አርከፈከፉት፡፡

“ጨዋታው ፈረሰ” ሲባሉ ልጅነታቸውን የተረዱት እያለቀሱ በእጀታቸው ጫፍ እንባቸውንና ሌላም ነገር እየጠራረጉ ፓርላማ ገብተውም የእፍርታሙን ጉልበተኛ የመለስን ተረት እየሰሙ መተኛት ጀመሩ፡፡ ወያኔ ሁሉ ነገር እረጭ ሲልለት እንደገና ተመልሶ ሌላ ምርጫውን የሚያሸንፍበት ዘዴ ተልሞ ኑ የምርጫ ጨዋታ እንጫወት የሚለውን ቀልዱን እንደገና ይዞ ብቅ አለ፡፡ የመጪው የ2002 ምርጫ ገና ባልሻረው የ1997 የምርጫ ቁስል ላይ ለመግባት የተዘጋጀ የይሉኝታ ቢስ ባለጌ ጭራሮ ነው፡፡ መለስ ዜናዊ ለነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ወሳኝ የሆኑትን ተቋማት ብቸኛ ተቆጣጣሪ ሆኖ በተደረገ የ1997ቱ ምርጫ የደረሰባቸውን ስቃይ በሚገባ የሚያስታውሱ ዜጎች አሁን መለስ እያቀረበ ላለው ፌዘኛ የ2002 የምርጫ ጨዋታ ጥሪ ምላሻቸው ምን ሊሆን ይገባል? ግንቦት 7 ለዚህ መለስ አለው፡፡

*ዴሞክራሲ የሃገራችን ህልውና ማስጠበቂያ፣ የመብታችን ማስከበሪያ፣ የብልጽግ ማምጫና የሰላማችን ዋስትና ነው፡፡ ይህን ክቡር ጉዳይ ጨዋታ አድርገን አናየውም፡፡ ነጻና ፍትህዊ ምርጫ የሚካሄድበት ሁኔታ ምን መምሰል እንደሚገባው ምርጫ 97ን ተከትሎ ከቀመስነው መከራ በተግባር ተምረናል፡፡ ዛሬም ወታደሩን፣ ስለላውን፣ ፖሊሱን በኪስህ ይዘህ፤ ቀንና ማታ በቴሌቢዘኑ መስኮት እንዳሻ እየተጎማመልህ፤ ካድሬዎችህን በምርጫ ቦርድና በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ ሰግስገህ፤ ኑ የዴሞራክሲ እቃ እቃ እንጫወት የሚለውን ቀልድህን ተወው፡፡ እኛ ሁሉንም ዜጎችና ፖለቲካ ድርጅቶች በእኩልነት የሚስተናግዱ፣ የህዘብን ፍላጎት የሚስከብሩና የሚከላከሉ ተቋማት ላሉበት ዴሞክራሲያዊ ሂደት መጀመር የጀመርነውን ትግል እንቀጥላለን፡፡ ይህንን መሰረታዊና ቁልፍ የሃገራችንን የዴሞክራሲ ችግር መፍታት በተናጠል ይሁን በጋራ ለሚታገሉት ኃይሎች በሙሉ ድገፋችን እንሰጣለን፡፡ ዴሞክራሲ ምርጫ ብለህ ምርጫን የዜጎችን የፖለቲካ እምነት መሰለያ ወጪ የሌለው መሳሪያ አድርገህ ሰልለህ ከእርሻችን፣ ከንግዳችን፣ ከሥራችን ከመሥሪያ ቤታችን እንደአውሬ መግቢያ እስክናጣ አደንከን፤ አሳደድከን፡፡ ያ አይበቃህም??? መለስ ሆይ የምትበላውን ብላ አንዴ የተበላነው ይበቃናል፡፡* ሊሉት ይገባል እንላለን፡፡

## በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የኑሮ ሁኔታ ሕዝብን ለአመጽ እያነሳሳ መሆኑ ተዘገበ

የግንቦት 7 የመረጃ አገልግሎት በአዲስ አበባና በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች ተዘዋውሮ ያሰባሰበው መረጃ የፍትህ እጦት፣ የአስተዳደር ብልሹነት እና የኑሮ ውድነት ሕዝቡን ክፉኛ በማስመረሩ በማንኛውም ትንሽ ሰበብ ሕዝባዊ አመፅ ሊነሳ የሚችል መሆኑን ያመለክታል ተባለ።

የኑሮው ውድነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ መሄዱን፤ በተለይም አዳዲስ በሚፈጠሩ የትግራይ ተወላጅ ሃብታሞችና በቀሪው የአገሪቱ ሕዝብ መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት እጅግ እየሰፋ መምጣቱን የተሰባሰበው መረጃ ያሳያል። ወያኔዎችና ለወያኔ ያደሩ አድርባዮች የሚሰሩት ቤት፣ የሚነዱት መኪና እና እየኖሩ ያለው ኑሮ ከኢትዮጵያ ድህነት ጋር ፈጽሞ የማይመጣጠን ሲሆን ትግራይን ጨምሮ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በቀን አንድ ጊዜ እንኳን ለመብላት ከማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ሕዝባዊ አመጹ በማንኛውም ሰዓት ሊቀሰቀስ እንደሚችል መረጃዎች ያመለክታሉ።

የመረጃው ተንታኞች በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ 55 ብር መሸጡ ኅብረተሰቡ ለአመጽ ማነሳሳቱን አስታውሰው ዛሬ ከሽህ ብር በላይ መሸጡ ሥርዓቱን ለተመሳሳይ ህዝባዊ አመፅ ያዘጋጃል ብለዋል።

ሕብረተሰቡ ከምግብ እቃዎች በተጨማሪ በሌሎች የፋብሪካ ውጤቶች ዋጋ መናርም እጅግ እየተሰቃየ መገኘቱን የጠቀሰው ይኸው ጥናት ኢትዮጵያውያን ከሞቃዲሾ ነዋሪዎች ባልተናነሰ ችግር ውስጥ እንደሚገኙ ጠቅሷል።

በቡድኑ ጥናት መሰረት የወያኔ አባል ባለመሆናቸው በርካታ የመንግሥት ሠራተኞች እንደሚባረሩ፤ ተማሪዎች ተመርቀው ሥራ ማግኘት እንደማይችሉና ይባስ ብሎም በግል ተወዳድረው ሥራ እንዳይዙ የትምህርት ማስረጃቸው እንዲያዝባቸው ትእዛዝ መተላለፉ የሥራ አጡን ቁጥር ከመቼውም ጊዜ በላይ ያናረው ሲሆን በአገሪቱ ታይቶ የማይታወቅ ማኅበራዊ ምስቅልቅል ሊፈጠር እንደሚችል ተንብዮዓል። በአንዳንድ መሥሪያቤቶች ዜጎች በ ቪፒአር ስም እየተባረሩ ሲሆን በምትካቸውም የወያኔ ታማኝ ካድሬዎች እንዲገቡ እየተደረጉ ነው።

በሌላ በኩልም የፍትህ እጦት ከመቼውም ጊዜ በላይ ጣራ መንካቱን ያመለከተው ይኸው መረጃ ዜጎች አንዴ የቅንጅት፣ ሌላ ጊዜ ድግሞ የኦነግ፣ አሁን ደግሞ የግንቦት 7 አባላት ናችሁ እየተባሉ እንደሚታሰሩና እንደሚሰቃዩ የቡድኑ ጥናት አመልክቷል። በወያኔ የሚደርስባቸውን አፈናና እንግልት ለመሸሽም በርካታ የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የኦጋዴንና የመሃል አገር ወጣቶች የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ በመቃወም የትጥቅ ትግል የሚያደርጉ ሃይሎችን በመቀላቀል ላይ መሆናቸውም ተገልጿል።

በተያያዘ ዜናም አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞች «ዘመዶቻችሁ የግንቦት 7ት አመራር አካል ናቸው» በሚል ሰበብ እየተባረሩ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ ሰው «እኛ ለልማት ደፋ ቀና ስንል የእናንተ ወንድሞች ልማትን ለማውደም ሴራ ሲጎነጉኑ ያድራሉ። ስለዚህ እናንተን ተሸክመን የምንጓዝበት ሁኔታ ስለማይኖር ከዛሬ ጀምሮ ሥራችሁን መልቀቅ ይኖርባችሁዋል» ብለው እንዳሰናበቷቸው ገልጸውልናል። እኚህ ሰው ሲናገሩ ስራ ከለቀቁ በኋላም በርካታ ማስፈራሪያዎች እየደረሷቸው መሆኑን ተናግረዋል።

## በቃሊቲ እስር ቤት ሴት እስረኞች በታይፎይድ በሽታ እየተጠቁ ነው

ከቃሊቲ በደረሰን ዜና መሠረት በአንድ አነስተኛ ክፍል ውስጥ ከአንድ መቶ በላይ የሴት እስረኞች ሲኖሩ በሁለተኛውና የተሻለ ነው በሚባለው ክፍል ውስጥ ደግሞ ከ 70 በላይ የሴት እስረኞች ይገኛሉ።በዚህ ንፅህና በጎደለውና በታፈነ እስርቤት ውስጥ ያሉት እህቶቻችን በታይፎድ በሽታ የታመሙ መሆኑን ተዘግቧል።

በቅርቡ ፕሪዝን ፌሎውሺፕ በመባል ከመለስ ጋር ቅርበት እንዳለው በሚነገርለት እና የአገር ሽማግሌ ነኝ በሚለው በፓስተር ዳንኤል  በሚመራው ድርጅት ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ተሰርቷል የሚባልለት የሴቶች እስር ቤት ውስጥ እንዲህ አይነት ወረርሺኝ ከተከሰተ ቁጥራቸው ከአራት መቶ በላይ እስረኞች በአንድ ክፍል ውስጥ የሚታጎሩበት የወንዶች እስር ቤት ውስጥ ሊደርስ የሚችለውን መገመት አያስቸግርም።

በእስር ላይ ያሉትን ወገኖቻችንን ከዚህ ወረርሺኝ ለመታደግ ለዓለም አቀፍ-ቀይ መስቀልና ለዓለም የጤና ድርጅት ድምፃችንን በጋራ ማሰማት እንዳለብን አስተያት ሰጪዎች ተናግረዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org